## *መመሪያ ቁጥር ገባ/2/2001*

## *በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የደረጃ “ሀ” ፣ “ለ” እና “ሐ” ግብር ከፋዮችን ግብር በግምት ለመወሰን የወጣ መመሪያ*

1. *አጭር ርዕስ*

*ይህ መመሪያ "በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የደረጃ “ሀ” ፣ “ለ” እና “ሐ” ግብር ከፋዮችን የግብርና ታክስ በግምት ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር ገባ /2/2001 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።*

2. *አውጪው ባለሥልጣን*

*የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገቢዎች ባለሥልጣንን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 121/1998 አንቀጽ 17 ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን መመሪያዎች ለማውጣት ስልጣን በተሰጠው መሰረት ለሙከራ ትግበራ ወቅት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።*

3. *የመመሪያው የተፈጻሚነት ወሰን*

*ይህ መመሪያ ተፈጻሚ የሚሆነው በአማራ ብሔራዊ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 4/1995 የደረጃ “ሀ” ፣ “ለ” እና “ሐ” ግብር ከፋዮች ተብለው የተመደቡ ግብር ከፋዮች ባገኙት ገቢ ላይ ሊከፈል በሚገባው የገቢ ግብርና ታክስ ላይ ይሆናል።*

4. **ትርጓሜ**

*“ባለ ኮሚሲዮን” ማለት ራሳቸውን የቻሉ ተግባረኞች ሆነው አበል ለማግኘት ባለ ኮሚሲዮን ስለአደረጋቸው ሰው በራሳቸው ስም ሸቀጦችን ወይም የሚንቀሳቀሱትን ዕቃዎች ወይም ማናቸውንም እነዚህን የመሳሰሉ ዕቃዎችን ለመግዛት ወይም ለመሸጥ የዚሁ ዓይነት ሥራ የሚሰሩ ወይም ማጓጓዣ ውል ለመዋዋል ግዴታ የሚገቡ ሰዎች የንግድ ማህበሮች ናቸው።*

## ክፍል አንድ

## የደረጃ “ሐ” ግብር ከፋዮች የግብር አወሳሰንና አሰባሰብ

5. **የግብሩ አወሳሰን**

1. በተሽከርካሪዎች፣ በጥብቅና እና በወፍጮ አገልግሎቶች የተሰማሩ ግብር ከፋዮች ሆነው ዓመታዊ ጠቅላላ የሽያጭ ገቢያቸው ብር 100,000 እና ከዚያ በታች ከሆነ ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በሆነው ሠንጠረዥ 4 መሠረት ግብር ይከፍላሉ፡፡

2. በሌሎች የንግድ ሥራዎች የተሰማሩ የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች የግብር የስሌት መሠረት የሚሆነው በአማራ ብሔራዊ ክልል የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮችን ዓመታዊ ገቢ ለመወሰን በተደረገው የመደበኛ ቁርጥ ግብር ጥናት በተወሰነው የጊዜ ቆይታ ውስጥ የተጠና ዓመታዊ ጠ ቅላላ የሽያጭ ገቢ ሆኖ፣ ግብር ከፋዩ ከተለያዩ የንግድ ሥራ እንቅስቃሴዎች ያገኘው ዓመታዊ ጠቅላላ የሽያጭ ገቢ ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በሆነው ሠንጠረዥ 2 መሠረት በአንድ የንግድ ዘርፍ የሚጠቃለል ከሆነ በእነዚሁ ሠንጠረዦች መሠረት ግብር ይከፍላል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተገለፀው ቢኖርም ግብር ከፋዩ ከተለያዩ የንግድ ሥራ እንቅስቃሴዎች ያገኘው ዓመታዊ ጠቅላላ የሽያጭ ገቢ በሠንጠረዥ 2 ወይም ሠንጠረዥ 4 መሠረት በአንድ የንግድ ዘርፍ መጠቃለል (መጣመር) የማይችል ከሆነ በሠንጠረዥ 1 እና/ወይም ሠንጠረዥ 4 በተመለከተው ውስጥ በየዘርፉ የሰፈረውን ግብር የሚከፈልበት ገቢ በማጣመር ግብሩ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 76/1994 አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 2 ሥር ባለው ሠንጠረዥ "ሐ" መሠረት ይወሰናል፡፡

6. **የተርን ኦቨር ታክስ አወሳሰን**

1. ከተርን ኦቨር ታክስ ነፃ ስለመሆን በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የተርን ኦቨር ታክስ ማስከፈያ አዋጅ ቁጥር 83/1995 አንቀጽ 7 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በመደበኛ ቁርጥ ግብር ገቢ ጥናት መሰረት ዓመታዊ የሽያጭ ገቢያቸው ብር 20,000 እና ከዚህ በታች የሆኑ በአገልግሎት ንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ግብር ከፋዮች የተርን ኦቨር ታክስ ባከናወኑት የሽያጭ መጠን ላይ በመመስረት ይሰላል፣

2. ሌሎች የደረጃ “ሐ” ግብር ከፋዬች የተርን ኦቨር ታክስ ውሳኔ በየንግድ ዘርፉና በየገቢ እርከኑ በተቀመጠው ከፍተኛ ጣሪያ መሰረት እየተሰላ እንዲከፍሉ ይደረጋል፡፡

7. የግብሩ አሰባሰብ

1. እያንዳንዱ የደረጃ “ሐ” ግብር ከፋይ የግብር ዘመኑ እንዳለቀ እስከ ሐምሌ 30 ድረስ የሚፈለግበትን ግብር/ታክስ ገቢ ሰብሳቢው ጽ/ቤት ወይም እሱ በሚወክለው ሶስተኛ ወገን ቀርቦ መክፈል ይኖርበታል፡፡

2. ግብር ከፋዩ ሊከፍል በተጠየቀው ግብር ካልተስማማ ቅሬታውን በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 76/1994፣ የተርን ኦቨር ታክስ ማስከፈያ አዋጅ ቁጥር 83/1995 እና እንዲሁም ኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 103/1996 ባሉት ድንጋጌዎች መሠረት እንደአግባብነቱ ለገቢ አሰባሰብና አወሳሰን ባለሙያዎች ወይም ለይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ማቅረብ ይችላል፡፡

3. በአንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው እንዳለ ሆኖ በግብር ዘመኑ አዲስ የመደበኛ ቁርጥ ግብር ገቢ ጥናት የተካሄደበት ጊዜ ከሆነ ወይም ከዚህ ጊዜ ውጭ አዲስ ግብር ከፋዮች ሆነው ገቢዎቻቸው በገቢ አሰባሰብና ክትትል ባለሙያ የተጠናላቸው ግብር ከፋዮች እስከ ሐምሌ 30 ባለው ጊዜ ውስጥ ገቢ ሰብሳቢው ጽ/ቤት በመገኘት ገቢያቸውን አውቀው የመክፈልና ገቢ ጽ/ቤቱ ደግሞ አጥንቶ የወሰነውን ገቢ እና ሊከፍሉ የሚገባውን ግብር የማሳወቅ የጋራ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

8. መቀጫ

1. አዲስ የመደበኛ ቁርጥ ግብር ጥናት የተካሄደበት የግብር ዘመን በመሆኑ ወይም ከዚህ ጊዜ ውጭ አዲስ ግብር ከፋዮች ሆነው ገቢያቸው በገቢ አሰባሰብና ክትትል የተጠና ሆኖ በአማራ ብሔራዊ ክልል መንግሥት የተርን ኦቨር ታክስ ማስከፈያ አዋጅ ቁጥር 83/1995 አንቀጽ 37 መሠረት የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች በዚህ መመሪያ መሠረት የሚወሰነውን ግብር እስከ ሐምሌ 30 ባለው ጊዜ ውስጥ ገቢ ጽ/ቤቱ ቀርበው ገቢ ሰብሳቢው መ/ቤት ገቢያቸውንና መክፈል ያለባቸውን ግብር/ታክስ ካላሳወቃቸው የገቢ ግብር እና የተርን ኦቨር ታክስ ክፍያን በጊዜው ባለመክፈል በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 76/1994 እና በተርን ኦቨር ታክስ ማስከፈያ አዋጅ ቁጥር 83/1995 መሠረት ከሚከፈል ወለድና ከሚጣል መቀጫ ነፃ ይሆናሉ፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለፀው ቢኖርም አዲስ የመደበኛ ቁርጥ ግብር ጥናት/አወሳሰን በተካሄደበት ጊዜ እንዲያውቁት የተደረገውንና መክፈል ያለባቸውን ግብር/ታክስ በጥናቱ የተወሰነው የገቢ ግምት ቆይታ ጊዜ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የግብር ዘመኑን ግብርና ታክስ እስከ ሐምሌ 30 ባለው ጊዜ ውስጥ መክፈል ካልቻሉ በገቢ ግብር

አዋጅ ቁጥር 76/1994 እና በተርን ኦቨር ታክስ ማስከፈያ አዋጅ ቁጥር 83/1995 መሰረት ወለድና መቀጫ ይጣልባቸዋል፡፡

3. የደረጃ “ሐ” ግብር ከፋዬች የስራ እንቅስቃሴያቸው በማደጉ ምክንያት ወደ ደረጃ “ለ” ወይም “ሀ” በሚሸጋገሩበት የመጀመሪያ የግብር ዘመን የሂ/መዝገብ የመያዣ ጊዜው ከቀጣዩ በጀት ዓመት ከሐምሌ 1 ቀን ጀምሮ መሆን ያለበት በመሆኑ መዝገብ ባለመያዝ ቅጣት አይመለከታቸውም፡፡

4. በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተጠቀሰው እንዳለ ሆኖ ሂሳብ መዝገብ እንዲይዙ ከተደረገበት ጊዜ በፊት ላሉት ጊዜያት በየወሩ ወይም በየሩብ ዓመቱ ታክሱን አሳውቆ ባለመክፈል የሚጣለው መቀጫም አይመለከታቸውም፡፡

## ክፍል ሁለት

## የደረጃ “ሀ” እና “ለ” ግብር ከፋዮች ግብር አወሳሰን

### *9. የግብር አወሳሰኑ የሚመለከታቸው*

1. በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 76/1994 እና ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በወጣው የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 4/1995 መሠረት በደረጃ "ሀ" እና "ለ" የተመደቡ ግብር ከፋዬች በሕግ በተሰጣቸው ጊዜ ውስጥ ተቀባይነት ያለው የሂሳብ መዝገብ በማቅረብ ገቢያቸውን አስታውቀው የማይከፍሉትን ይመለከታል።

2. በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው እንዳለ ሆኖ ግብር ከፋዬች በሕጉ በተሰጣቸው ጊዜ ውስጥ ሂሳብ መዝገብ የሚያቀርቡበትን ጊዜ መጠበቅ ሳያስፈልግ የግብር ከፋዩን ዓመታዊ ገቢ የሚያሳየውን ሽያጭ የገቢ አሰባሰብና ክትትል ባለሙያዎች ክትትል አድርገው መረጃውን መያዝ ይኖርባቸዋል።በግብር ሕጉ በተቀመጠው ጊዜ ሂሳብ መዝገብ ካላቀረቡ ወይም የቀረበው የሂሳብ መዝገብ ተቀባይነት ካጣ ይህንን መረጃ በመያዝ ወዲያውኑ ወደ ግምት አወሳሰኑ እንዲገባ ይደረጋል።

## *10. ዓመታዊ ጠቅላላ የሽያጭ ገቢ ስለማግኘት*

ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ለግብሩ አወሳሰን መሠረት የሚሆነው ዓመታዊ የሽያጭ ገቢ፣

1/ ከተለያዩ አካላት የሚመጡ የግዥ ወይም የሽያጭ መረጃዎች ሲኖሩ መረጃው የሽያጭ መረጃ ከሆነ በተገኘው መረጃ፣ መረጃው የግዥ መረጃ ከሆነ የአካባቢውን የወቅቱን ገበያ መሠረት በማድረግ ወይም ተገቢው ጥናት ተደርጐ የወቅቱን ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ማግኘት ካልተቻለ በሚከተለው ቀመር በመጠቀም የተገኘው ዓመታዊ የሽያጭ ገቢ ይሆናል።

$$ሽያጭ = \frac{ግዥ}{100\text{-}ያልተጣራ\ ትርፍ\ በሽያጭ\ ላይ} \times 100$$

2/ ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በሆነው ሠንጠረዥ 5 ውስጥ የተዘረዘሩትን የአገልግሎት ዘርፎች በተመለከተ በሠንጠረዡ የተቀመጠው ዓመታዊ የሽያጭ መጠን ይሆናል።

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ከተገለፁት ውጭ ሆነው ግብራቸው ከ3ኛ ወገን በሚላክ መረጃ የሚወሰንላቸው ግብር ከፋዬች የግዥ ወይም የሽያጭ መረጃቸው ግብር በሚወሰንበት ጊዜ ቢዘገይና ግብር ከፋዩም ማቅረብ ካልቻለ የግብር ከፋዬ ዓመታዊ ገቢ በአንቀጽ 9 ተራ ቁጥር "2" መሠረት ግብሩ በግምት ተወስኖ ግብሩና ታክሱ እንዲሰበሰብ ይደረጋል።

4/ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 በተጠቀሰው መሠረት ግብር ከፋዩ ቀድሞ ከሚታወቀው ንግድ ዘርፍ ከሚያገኘው/ከተገኘው መረጃ በተጨማሪ ገቢ ስለመኖሩ አሳማኝ ሁኔታ ሲኖር ተጨማሪውን ዓመታዊ ገቢ በመገመት ወይም መረጃ ከሆነ መረጃውን ቀድሞ ከሚታወቀው ንግድ ዘርፍ ከተገኘው ወይም ከሚገኘው የግብይት መረጃ ጋር በማዳመር የሚገኘው ውጤት ጠቅላላ ዓመታዊ ሽያጭ ይሆናል።

## *11. ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ስለማግኘት*

1/ ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በሆነው ሠንጠረዥ 5 ውስጥ የተዘረዘሩትን የአገልግሎት ዘርፎች በተመለከተ በሠንጠረዡ የተቀመጠው ዓመታዊ የተጣራ ትርፍ ይሆናል።

2/ ሌሎች የንግድ ዘርፎችን በተመለከተ የተጣራ ትርፉ (ግብር የሚከፈልበት ገቢ) ግብር ከፋዩ ያገኘው ጠቅላላ ዓመታዊ ገቢ በዘርፉ በተሰጠው መቶ መተመኛ ተባዝቶ የተገኘው ውጤት ይሆናል።

3/ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተጠቀሰው ቢኖርም በጣምራ ግብር ለሚወሰንላቸው የተለያዩ ንግድ ዘርፎች እያንዳንዱ የንግድ ዘርፍ በራሱ የትርፍ መቶ መተመኛ ተባዝቶ/ተሰልቶ የሚገኘው ውጤት ግብር የሚከፈልበት ገቢ ይሆናል።

## 12. የገቢ ግብር አወሳሰን

1/ ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በሆነው ሠንጠረዥ 5 ውስጥ የተዘረዘሩትን የአገልግሎት ዘርፎች በተመለከተ በሠንጠረዡ የተቀመጠው ቁርጥ ግብር ይከፍላሉ። መዝገብ ባለመያዝ የሚጣለውና ሌሎች አስተዳደራዊ መቀጫዎች በሕጉ መሠረት ተሰልተው በተጨማሪ ይወሰናሉ።

2/ አሽከርካሪዎችና እረዳቶቻቸው ሊከፍሉት የሚገባው የሥራ ግብር በባለቤቶችም የሚሸከረከር ቢሆንም በሠንጠረዥ 5 የተቀመጠው ቁርጥ ግብር ሆኖ የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ እንዲከፈል ይወሰናል።

3/ ሌሎች የንግድ ዘርፎችን በተመለከተ በአንቀጽ 11 መሠረት የተገኘውን ግብር የሚከፈልበት ገቢ በመውሰድ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 76/1994 አንቀጽ 19 ሠንጠረዥ ሐ መሠረት ግብሩ ይወሰናል።

4/ ግብር ከፋዩች ገቢ ያገኙት ከተለያዩ ዘርፎች ከሆነ ከየዘርፉ የተገኘው ዓመታዊ ገቢ በትርፍ መቶ መተመኛው ተባዝቶ የተገኘውን ግብር የሚከፈልበት ገቢ በማዳመር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 በተገለፀው መሠረት ግብሩ ይወሰናል።

## 13. የተርን ኦቨር ታክስ አወሳሰንና አሰባሰብ

1. የተርን ኦቨር ታክስ ከፋይ የሆኑ የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋዮች በየወሩና የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች ደግሞ በየሦስት ወሩ ታክሱን አስታውቀው መክፈል ይጠበቅባቸዋል።

3. ዓመታዊ ታክስ የሚከፈልበት ገቢያቸው ከብር 500,000 በላይ ሆኖ ለተጨማሪ እሴት ታክስ መመዝገብ ሲኖርባቸው ያልተመዘገቡ ግብር ከፋዮችን በተመለከተ ለተጨማሪ እሴት ታክስ መመዝገብ ስላለባቸው የገቢ ግብሩንና ተርን ኦቨር ታክሱን እንዲከፍሉ ከተደረገ በኋላ ለተጨማሪ እሴት ታክስ በግዴታ እንዲመዘገቡ ሆኖ ዝርዝራቸው ከሙሉ የምዝገባው ማስረጃ ጋር ለባለስልጣኑ መ/ቤት ሪፖርት መደረግ ይኖርበታል።

## 14. ስለ ባለኮሚሲኖች

በንግድ ወኪልነት ሳይሆን አበል /የኮሚሽን ጥቅም/ ለማግኘት ባለ ኮሚሴዮን ስለአደረጋቸው ሰው የሚሰሩ ግብር ከፋዬች ለዚሁ ሥራ የንግድ ፈቃድ ያላቸው ከሆኑና ባለ ኮሚሲዬን ካደረጋቸው ሰው ጋር በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2203 ወይም 2205 መሠረት ውል ፈፅመው በኢትዮጱያ ንግድ ሕግ ቁጥር 166/1952 ምዕራፍ 4 በተዘረዘሩት ድንጋጌዎች መሠረት እየሰሩ መገኘታቸው ሲረጋገጥ ባገኙት የኮሚሽን መጠን ግብሩንና ታክሱን እንዲከፍሉ ይደረጋል።

## 15. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት የነበሩ የግብርና ታክስ ግምት አወሳሰን ጉዳዮች በጊዜው ይሰራባቸው በነበሩ መመሪያዎች የሚፈፀሙ ይሆናሉ

## 16. የተሻሩ ድንጋጌዎች

ይህ መመሪያ ተፈጻሚ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ ቀደም ሲል የነበሩ የግብር እና ታክስ አወሳሰን መመሪያዎች በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፡፡

## 17. መመሪያው ተፈጻሚ የሚሆንበት ቀን

ይህ መመሪያ የካቲት 1/2001 ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል።

የአማራ ብሄራዊ ክልል መንግስት

ገቢዎች ባለሥልጣን

<u>ባህር ዳር</u>